# ሕልምና ስኬት

Thank you very

## የግጥም መድብል

ከሙሉመቤት ገ/ዮሐንስ

ሚያዝያ 2003

መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው።

All rights Reserved 2011

የመጀመሪያ እትም 2003 ዓ.ም

ከቨር ዲዛይን ጺዮን ጌታቸው

# ምስጋና

በቅድሚያ ከሞት ላተረፈኝና ለዚህ ላደረሰኝ እንዲሆም አስጀምሮ ያስጨረሰኝን ልዑል እግዚአብሔር በእጅጉ አመሰግናለሁ።

ይህቺን የግጥም መድብል አዘጋጅቼ ለህትመት እንዳበቃት ላበረታቱኝ፣ የሞራል ድጋፍ ለሰጡኝና ጉልበት ለሆኑኝ ለዶ/ር ናይክ ሠናይ፣ ለወ/ሮ እታለማሁ ፍቅሬ እና ለወ/ሮ ጽጌ ይገዙና ባለቤታቸው እንዲሁም ለልጆቼ በሙሉ በተለይ ደግሞ በዳላስ ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን የንግድ ማኅበረሰብ ወዳጆቼና ጓደኞቼ ልባዊ ምስጋናዬን ለማቅረብ እወዳለሁ።

የመጽሐፋን ህትመት እውን ትሆን ዘንድ በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ በርካታ ሰዎችን በማነጋገርና በማስተባበር ከፍተኛ ዕገዛ ላደረገልኝ ወንድሜ ለአቶ ጌታቸው ገ/ዮሐንስ አድናቆቴን እገልጻለሁ።

ባላቸው የሥነ ግጥም ችሎታና ዝንባሌ የመጽሐፏን ረቂቅ በማንበብ እርማትና ገንቢ አስተያየቶችን ለሰጡኝ ለአቶ ወንድወሰን በየነ ከፍ ያለ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ።

ይህቺን መጽሐፍ አዘጋጅቼ እስክጨርስ ድረስ ጊዜአቸውን መሰዋዕት ላደረጉልኝና በኮምፒውተር ጽሑፋን ያለመሰልቸት የሰሩትን ወ/ሮ የምሥራች ጥላሁን ከልብ አመሰግናቸዋለሁ።

በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለመጽሐፏ ህትምት ዕውን መሆን ድጋፍና ትብብር ላደረጉልኝ ሁሉ በአጠቃላይ ይመስገኑልኝ።

ሙሉመቤት ገ/ዮሐንስ

# ውጪያዊ ማንነት

መለኪያው ምን ይሆን የማንነት ትርጉም
ቁመት ነው ቁንጅና ወይስ ደግሞ ቀለም?
ወይስ የቀይ ዳማ ቅላትና ጥቁረት
በሥጋ መተለቅ ውፍረትና ግዝፈት?
ይሆን ቀጠን ብሎ ረዘም ያለ ቁመት
የዕድሜ መጨመር፣ የፀጉር መሸበት
የቱ ይሆን መለኪያው የሰው ሰውነቱ
መልካም ሥራ ሠርቶ የሚያሰኘው አንቱ?
የሰው ልጅ ማንነት ከውስጥ ካልወጣ
ላይ ላዩን ቢያሣምር ሲገባ ሲወጣ፤
ቢማር ቢመራመር ቢሞላ በጥበብ
እኔ የማምንበት የማሰፍረው ነጥብ፤
ስለ ውበት ሳይሆን ስለ ሰው ቁንጅና
በውጪ ሰውነት መልክና ቁመና፤
ፀባይ ቁምነገር ነው የሰው መመዘኛ
ማንነት መለኪያው ባለባበስ ሳይሆን
የውጪውን አካል ግርዶሽ አርጐ መልክን
መልክን ግርዶሽ አርገው የውጭውን አካል
ንፁህ ቅን አሳቢ ራስን በማስመሰል
ስንቱን አሰቃይቶ ስንቱን በማታለል
ብዙ ጨካኝ አለ አጉል ጨዋ መሰል::
ደግሞ በሌላ አንፃር ውጪው ያላማረ
እንዲሁ ሲታዩ በውጭ አካላቸው
በጨካኝ ወንበዴ ስንፈርጃቸው

መልካም በጐ ሥራ ሆኖ ተግባራቸው
ውስጣቸው ያማረ ብዙ ሰዎች ናቸው።
የውስጥ ነፀብራቅ ካልወጣ በኢፋ
ውጭን በማሣመር ቢዘከር ቢለፋ
ራስን ማታለል ነው በሐሰት ልፍለፋ።
በዝና ደንዝዞ ለማስመሰል ቢጥር
በጉራ ቢፎልል ምን ቀመናው ቢያምር
ከውስጥ ከሌለ ዝንተ ዓለም አይሠምር።

## ሕልሜ

ያለፈውን ሕልሜን ስቃኝ
አሁን ደግሜ አየሁኝ
በሕልሜ አንድ ቀን ማታ
በቅዠት መሃል ሸውታ
የሚያመለክት እውነታ
የምኞቴ ማዕድ ገበታ
ሲሆንልኝ ስበረታ
በርቺ የሚለኝ ሰው ባጣ
አምላኬ ሲሆነኝ መከታ፤
የልጅነት ውጥን ሥራ
የሕልሜ መገለጫ ጀመረ ጮራ
የእድሜ ልክ አዝመራ
እንዲኖር ሲታወስ ሲወራ፤
መፅሐፌ ታላቅ ሚና አላት
ሕይወቴን አስታዋሽ ዘካሪ ትንግርት
አዎ መፅሐፌ ሃውልቴ ናት።
ባልፍ እንኳን ማስታወሻዬ



ምኞቴ (ሙከራዬ) እንዳይቀር ባጭር
አለብኝ መዋተት መፍጨርጨር
ወረቀቴን ማገናኘት ከብዕር።

## የአሜሪካ ኑሮ

እኔ የሚገርመኝ የአሜሪካ ኑሮ
ሌት እንቅልፍ ሳይኖር ቀን እረፍት ታጥቶ
ወገብ ተንቀጥቅጦ እግር ተብረክርኮ
በሣምንት አምስት ቀን ስድስት ቀን ተሠርቶ
ደስታ የሚባል ነገር ከአእምሮ ጠፍቶ፤
የሚያስቀው ነገር ሲያስኮርፍ እያየሁ
እረ ፍስሃ የታል ሣቅ ወዴት ነው ያለው
ፈልጌ አስፈልጌ አልቻልኩም ላገኘው።
ቤተሰብና ልጅ ባንድ ቤት ቢሮሩም
ለእግዛብሔር ሰላምታ ሊገናኙ አልቻሉም።
አንደኛው ሲነሣ ይተኛል አንደኛው
መልእክት እንኳን ቢኖር ያው በወረቀት ነው።
ለስሙ ባንድ ቤት ባንድ ጣሪያ እየኖርን
ልጆቼ ናፈቁኝ እረ መላ በሉኝ
እነሱ ሲገቡ እኔ እየወጣሁኝ።
በአሥራ አምስት ቀን አንዴ በአይን ከተያየን
ማዘርዬ እዴት ነሽ ጠፋሽ ተባብለን
ሌላ ሁለት ሣምንት ደግሞ እንጠብቃለን
እንዳንዴ የአመት በዓል ካላሰባሰበን
ወርም እቆያለሁ ናፍቁ ልጆቼን።
ወይ ባገር ቤት ሆኜ በቀጭኑ ሽቦ

ሁሉም በየሠርጉ በተበረሁበት
ማየቱ አልቀረም እንዲህ ያለ ስህተት፡፡
በመጨረሻውም እኔ የማክለው
ለወገን ወዳጆቼ የማስተላልፈው
ትዝብቱን በምክር እንዲያስተውሉት ነው
ጅንስንም ብንለብሰው በቦታው መልካም ነው
ሱፋም ለሠርገኛው ክብርና ውበት ነው
ሁሉን በየፈርጁ ያምራል ብንለብሰው፡፡

2010

## ስደት

በተወለድንበት ባደግንባት አገር
ጭቃ እያቦካን እንጀራ ስንጋገር፤
ባልና ሚስት ሆነን ቤት ከአሸዋ ሠርተን
ሶኒ ከእሽክርክሪት ከጭቃ ጀበና
እንደእናቶቻችን እያፈላን ቡና
የውሸቱን ቡና እውነት አስመስለን፡፡
እትዬ እታፈራሁ እትዬ በለጡ
ቡናው ፈልቷልና ኑና አቦሉን ጠጡ፡፡
እየተባባልን ቡና ቁርስ አቅርበን
በድንጋይ በርጩማ ደርድረን ተቀምጠን
ወሬ እያወራን ዘፈን እየዘፈን
መንደር ተሰብስበን ከጧት እስከማታ
እንጫወት ነበር እቃ እቃ ጨዋታ፡፡
የዛሬው ይመጣል ብለን መቼ አሰብን
የትም ርቀት ሆና ከአዲስባ ሐረር
ለባሕሽን ስንሄድ እንላቀስ ነበር፡፡



## ሐረር

ያች ሜዳ ጋራ ሸንተረር
ሸንኮር ያደከባት ውቢቷ ሠፈር
ዛፍ ለዛፍ ተንጠልጥዬ እንደወፍ
እንደ ዝንጀሮ ስዘል ከቅርንጫፍ ቅርንጫፍ፤
ግንዱ ላይ ቆሜ ፍራፍሬ ስንወራወር
ዘይቱና ወሽመላ፤ ማንጎና ቴምር
ለምለሟ መሬት የፍራፍሬ ሙላት
የአትክልትና የቡናውን ምርት
የማንጎ የጊሸጣ ደግሞም የመንደሪን
የሙዝ የቲኒና የብርቱካኑን
አማርጬ የበላሁባት መሬት
ወንዝ ወርጄ የዋኘሁባት
ጋራ ወጥተን ስንለቅም እንጨት፤
ድንጋይ ላይ ቆመን ስንወራወር
ተልከን በእግር ስንበር
ስንመለስ ተሽቀዳድመን
ይች ምራቅ ሳትደርቅ ተብለን
ድካም ሳይታይብን
ከብቶች ለማገድ ስንወጣ ስንወርድ
በሩጫ በዝላይ ስንወራረድ
በትግል በቦክስ ስንፈታተሽ
ስንሯሯጥ ስንቀድም ስንሸሽ
ከብቶች ሲጠፉ ሳናያቸው ስንጫወት
ቡቃያ በልተው አጥር ፈንቅለው
በአፈላማ ተያዘው፤

ሲሰሙ ወላጆቻችን
አለንጋ ይዘው እያባረሩን
ይዘው በአርጩሜ ሲሰበልቡን፤
አንቺ የኔነሽ አንተ የሌላው
እያባበሉም ሁሉም ወላጅ ነው።
አብረን ተገርፈን አብረን አልቅሰን
ቤተሰብ ሆነን ወንድምና እህት
ክፉና ደጉን ያለየንበት
ደስታና ፍቅር ያሳለፍንበት
ደግሞ ቢገኝ ልጅነት
ምን ባስበው በምናብ ቆሜ
ተመልሶ አይመጣ ያ ዕድሜ።

## አፋልጉኝ

አንድ ቀን ሳልፍ በጐዳና
አንዷን ጭልፊት አየሁና
ልቤ ተነካ በውበቷ
ከቶ አስጠላችኝ የቤቷ
ቤቷም አስጠላኝ ልጆቿ
ከአብራኳ የወጡት አለሞቿ
አመሌ ሆነ ፊቷን ማጥቆር
ቤቷ ስደርስ ከሰፈር
ሚስቴም ተገርማ በሁኔታው
ምን ነው ፍቅሬ ብትለኝ አወረድኩባት መዓቷን
ስለመሠላት ያመመኝ
በስሜት አስጠየቀችኝ
እኔም ብሶቴን በእልህ



ለሊትና ቀን ስጨፍር
ሚስቴን አስኬድኳት ከሃገር
ልጆቹን ይዛ ተክዛ
ከቤቴ ወጣች አልቅሳ
እኔም ጭልፊትን ሳዝናና
ገንዘቤም አልቆ ቀረሁ መና
ጭልፊትም ስታይ ሁኔታዬን
ገንዘቤ አልቆ እጄ ማጠሩን
በልቻው እንግዲህ የኔ ፍቅር
ስለሰለቸኝ አገር ልቀይር
አለችና በጭካኔ
ገለል አለች ከጐኔ
ስልክም ደውዬ ባናግራት
አታፍርም እንዴ የልጆች አባት
ይልቅ ፈልጋት ሚስትህን
ሁሉንችላ ያኖረችህን
ነገ በኔም ሳይደርስብኝ
ካንተ መሸሽ አለብኝ ብላ አሾፋብኝ
ብን አለች ካጠገቤ ከሁለት ያጣ አድርጋኝ
አሁን ሥራዬ ቆጨኝ እስቲ ሚስቴን አፋልጉኝ
ሕግ አፍርሼ የሠማዩን
ቃልኪዳኔን ጥሼ የምድሩን
አንድ ለአንድ መባባሉን
ይኸው አሁን ተፀፀትኩኝ
በምን አይኔ ልያት ሚስቴን
የሁለት ልጆች እናቷን።
ግንድ ያለህ የሽማግሌ

## መሠናክል አንሁን

መስራት የማይወዱ
መጀመርን እንጂ መጨረስ አይችሉ
ወይ ፀንተው አይቆሙ ወይ አይከተሉ
እንቅፋት የሆኑ ብዙ ሰዎች አሉ
መቻቻል መታገስ ያልለመደባቸው
ጥቂት ሠርተው ማቆም ችግር ሲገጥማቸው
ትንሽ ጋደል ሲል ማጣፊያው ሲያጥራቸው
ለኛ ይሁን ሳይሆን ለኔ ልማዳቸው፤
ጥሩ ልምድ ለሰው የማያካፍሉ
የዕድሜ ባለፀጋ አዛውንት ሳይሉ
ለታላላቆቻቸው ክብርን ከማይሰጡ
ለራስ ብልፅግና ከሚሽቀዳደሙ
በተግባር መርምረው ሀቁን ሳይረዱ
በቃላት ሽንገላ አምነው አይገዱ።

## የእኛነት ደላመድ

በአንድነት ተሠርቶ
በእኛነት ውጤት
አንድም ተመካክሮ
አሊያም አብሮ በሮ
አንዱ ኋላ ሲቀር
ሌላው ቀድሞ ሮጦ፤
ውጤት ለማስገኘት
መስራት ነው በእኛነት።



እንዲህ እኛና እናንተ
ሁለትም ሆነን ሦስት
ማስለመድ አለብን ትጋትና አብሮነት
ደግሞ ተመካክረን እያሳየን ኅብረት
አንዱ ደከም ሲል አንዱ እያበረታ
ለእኛ ብለን እንሩጥ የኔነት ይገታ።
ለሃገራችን ዕድገት ለውጥ ለማምጣት
ምሳሌ ለመሆን እናሳይ ጥረት
ቢጣፍጥ ቢመርም አብረን ተመካክረን
ክፋት አስወግደን ቅንነት አንግበን
ወገንን ለመርዳት አገርን ወክለን
በአንድነት እንሥራ እጅና ጓንት ሆነን።

## ለምን?

እግዚአብሔር በአምሣሉ የፈጠረውን ፍጡር
ሰው ምንም ባለፋበት
የራሱ ባልሆነ ንብረት
ዝንት አለም ቢኳትን
ሊሠራ ሊከፍል በማይችለው
የምድር ዳኛ የማይዳኘውን
ቅጣቱ በአለም ብቻ የማይቀር
እስከ ወዲያኛው ለሚሻገር
ሰው ግብዝ ነው ውስጠ መራር
የማይታዘዝ ለእግዚአብሔር
እንደለፋበት ቁሳቁስ
የሰውን ገላ ማፍረስ።

መግደል፣ ክቡር አካልን ማጉደል
በራሱም ላይ መብት እንዳለው
ረስቶ አምላኩን እንደፈጠረው
ሕይወትን እንደዋዛ
በገንዘብ በአልማዝ እንደሚገዛ
ነፍስን ማጥፋት በራስ
ለምን አስፈለገ ሕግን ማፍረስ እኮ ለምን?
ሰው ሰውን የሚያፈቅረው
መጀመሪያ ራሱን ሲወድነው
ራሱን የሚጠላ ፍቅርን አይሠጥም ለሌላ።
ምን ጊዜም ጠፍቶ የሚተካ
ሕይወት ገንዘብ አይደለም ወይም ዕቃ
በሰው ልጆች ሕይወት መብት ያለው
የሠራው የፈጠረው
ባለቤቱ እግዚአብሔር ነው
ማዳን መግደል የሚችለው
በአጉል እልህ ተነሳስቶ
በሆነ ባልሆነው በመናቆር
ለራስ አይጠቅም ወይም ለሃገር ።

## የሕፃናት በደል

እስቲ ደግሞ ልቃኝ የሕፃናትን በደል
ግርፋቱንና የስድቡን ደውል
ያልዳበረ ሕፃን እንቡጥ ጽገሬዳ
ተፈጥሮ ያደለውን የአእምሮ ጓዳ
በጉጂ ንግግር እንደምን ይጎዳ?



በ10ኛ ወሩ ገና በልጅነት
ልጅን ማታለሉ ወፌ ቆመች ማለት
ሥራ ለማሠራት ጠንክሮ አድጉ ማየት
ቁንጥጫና ጥፊ አለንጋ እያሳዩ
የርህራሔ ስሜት ለልጅ ሣያሣዩ
እንዲህ አይነት ቅጣት አእምሮ የሚጐዳ
ምነው እናት አባት ሆኑ ለልጅ ባዳ
እንግዲህ እናት አባት ልጅ ስታሣድጉ
ርህራሔ ሰላም ፍቅር አትንፈጉ።

## የመንፈስ ጭንቀት

አንድ ሰው ተወልዶ ሲኖር በአለም ላይ
አለው ብዙ ሕልሞች አለው ብዙ ራእይ
ለመሆን የሚሻው ኑሮ ለማሣካት
ለማድረግ ያቀደው እስካለ በሕይወት
ተምሮ አጥንቶ እውቀትን ለማግኘት።
ይሻል የአዳም ልጅ ይሻል የሰው ፍጡር
መሆን ይፈልጋል ነጋዴ ኢንጅነር
የሥራ መስክ መክፈት ለወገን ለሃገር
ይሻል የሰው ፍጡር ማግባት መያዝ ትዳር
መውለድ ይፈልጋል ይሻል መተካት ዘር
ልጅ ማሣደግ መዳርማየት ወግ ማዕረግ
ማድረስ ለቁም ነገር።
በየሠራ መስኩ ተሠማርቶ መስራት
ራሱን አሸንፎ ቤተሰብን መርዳት
ሰው ካልተሣካለት በለስ ካልቀናው
ያን ሁሉ እቅዱን ውሃ ከበላው

ያልሰመረ እንደሆን ይህ ሁሉ ጥማቱ
ደስታው ይጠፋና ይበዛል ጭንቀቱ::
ጉዳቱን ከዘመድ ደብቆ ካኖረው
ለሰው ካላዋየው ጓደኛ ካላየው፤
በግሉ ውስጥ ውስጡን ይብሰለሰልና
ብቻውን ያወራል ከሰው ይርቅና::
በዚህ ጊዜ ያገር ልጅ ወይንም ዘመድ
ምን ሆነሃል ብሎ ደፍሮ ቢጠይቀው
ሃሳቡን ቢረዳው ቀርቦ ቢያወያየው
አትቸገር ወገን አለሁልህ ቢለው
ተስፋ ያገኝና ይድናል ሰውየው::
ዘመድ ካልጠየቀው ጓደኛ ካላየው
ለሰው ከሰው ሌላ ማነው የሚደርሰው?
ችግሩን ሳንጠይቅ ምክንያቱን ሳናውቀው
በቸገረው ነገር ሳንተባበረው
ስትረስ አለበት እብድ ነው ብንለው
የሕሊና ዕዳ የአእምሮ ፍርድ ነው::
ስለዚህ ሁላችን በዚህ አገር ያለን
እንጀራ ለማግኘት ከሃገር የወጣን
መቸገር አለብን ለወገኖቻችን::
መጠየቅ ይገባል ቀርቦ ማወያየት
ጭንቀቱ ሳይበዛ ሳይደርስ ወደ እብደት::
በሰው ሃገር ሆነው ከወገን ተለይተው
ያልፍልናል ብለው እንዳሰቡት ባይሆን
አይዟችሁ እንበላቸው ተባብረን ሁላችን::
ይኸነው እርዳታ ይኸነው መቆጨት
ለሃገር ልጅ መድረስ ማዳን ከጭንቀት::



## ሕልምና ስኬት

የብዙ አመት ሕልሜ እቅድና ራእዬ
ተወጥነው ኖረው በጨቅላ አእምሮዬ
ተሠራጭተውብኝ በመላ እኔነቴ
ፍርሃት አሸንፎት ሲከዳኝ ድፍረቴ
አመታት አለፉ ሣይወጣ ድርሰቴ::
ልፈታው እልና እቅድና ህልሜን
መንትያ ሃሣቦች ሆነውኝ አጠብቂኝ
አንደኛው ሃሣቤ በርቺ ፃፊ ሲለኝ
ተይው ጣይው ይላል ሌላው ሲያዘናጋኝ
በሕሊና ሙግት እራሴን ሲያዞሩኝ
ሕልሜ ሳይፈታ እስካሁን ቆየሁኝ::
በአንድ ሃሣብ ፀንቼ ለማስፋታት ሕልሜን
ሃሣቤን ሰብስቤ ጭሬ እጫጭርና
ፍርሃት ይይዘኛል መሃል እደርስና::
ካሣቤም አይወጣ ሕልሜ አይዳፈንም
ይቆይ ይቆይና ይመጣል አሁንም
ደብተሬን ገልጬ አንስቼ ብዕሬን
መፃፍ እጀምርና መሞነጫጨሬን
ወዲያ እጥለዋለሁ ሳስበው አቅሜን::
መላቅጡ ጠፍቶኝ ሣወርድ ሣወጣ
አይዞሽ በርቺ የሚለኝ ከጐኔ ሰው ሣጣ
ጠፍቶም እኮ አይጠፋ የኔ ሕልም ቅጥ አጣ::
ሣስበው እቅዴን ደግሞ ቁጭ ብዬ
እልሄ ይመጣና ይነሣል ወኔዬ::
ብቻ እንዲሁ እያልኩኝ ይህን ሁሉ ዘመን

ወደ ኋላ ቀረሁ ሣላስፈታው ሕልሜን።
ዛሬ ነገን ሲተው ቀን ሲተካ ሣምንት
ሣምንት ሲዋጥ በወር ወር ሲተካ አመት
የኔም ዕድሜ ሳላውቅ እንዲሁ እንደዘበት
ሄደ ገሠገሠ ምንም ሣልሠራበት።
አእምሮዬ ያለ እርፍት ማሠቡን ሳይገታ
ሕልሜን እንኳን በውን በገሃድ ሣልፈታ
ውስጥ ውስጡን ከንክኖኝ እረፍት ቢያሳጣኝም
መጽሐፌ ለወገን ቢመር ቢጥመውም
ይፋ ሣላወጣው እንዳለምኩ አልቀረም።

## ክሬዲት

በዚህ በአሜሪካ የሕጉ አስከፊነት
ትንሽ ሆነ ትልቅ ሰው ካጠፋ ጥፋት፤
ሕጉን ከደፈረ ከጣሰ ሥርአት
ተብሎ ይወራል የሰውም ክሬዲት።
አንድ ደብተር ሙሉ አትተው አትተው
ውለታ (deal) ነው ይሉህና ስቀው አስፈረመው፤
እንዷን መስመር በትስት ቀኗ ብታልፍበህ
ሕይወትህን ሙሉ ጥፋት እንደሠራህ
በየደረስክበት ይበዛል ሐጢያትህ።
አንድ ቦታ ሄደህ እቃ ለመግዛት
ወይም ለመኖሪያ ቤት መከራየት
በገዛ ገንዘብህ ከሌለህ ክሬዲት
አትችልም ብለው ያሣጡሃል መብት።
አንዴ ኮምፒውተር ውስጥ ስምህን ካስገቡት
ብቅ እያደረጉ ያለህን ክሬዲት
አትችልም ይሉሃል ናላህን ሲያዞሩት።
ጠጥተህ ብትነዳ ትንሽ ሞቅ ብሎህ
መስኪያውን ይዞ ፖሊስ ካጋጠመህ
መንጃ ፍቃድህን ጭራሽ ትቀማለህ።
ክሬዲትህ ጠፍቶ ይደራረብና
በእግርህ ትሄዳለህ መብትህን ታጣና።
መኖሪያውን ካጣ እንግዲህ አንድ ሰው
እሚላወስበት መኪና ከሌለው
የሕጉ አስከፊነት እያንገሸገሸው
ያው እንዳንዳንዶቹ ሆምለስ (ቤት አጥ) መሆኑ ነው።
እንግዲህ ወገኔ ካገርህ ከወጣህ
ያልፍልኛል ብለህ በአላማህ ከፀናህ
ሕግና ሥርአቱን ጠንቅቀህ አክብረህ
ከግብህ ለመድረስ መበርታት አለብህ።

## የአበላል ሥርዓት

በዚህ በአሜሪካ ባለንበት ሀገር
የምግብ ሥርአት ወይም ቴብል ማነር
የሚባለው ነገር ከቶም አይስተዋል
ምግብ በመንገድ ላይ ውሃ በእጅ ተይዞ
ወደ ሥራ ይኬዳል መኪናውን ይዞ
ቡና የሚጠጣው በማሽን ተፈልቶ
በየመኪናው ውስጥ ወተት ማኪያቶ
ቁጠማ ጀበና ስኒና ረከቦት
በማዕረግ ጉዝጓዝ ዘርግቶ በኢማን መጠጣት

ኢትዮጵያ ቀረ ካገር የወጡለት::
ጡልጡል እያሉ ፒዛ እየገመጡ
ድክምክም ብለው ሁለት ሥራ ሠርተው
ዝለው ቤት ሲመጡ
እንቅልፍ ይጥላቸዋል እንደተቀመጡ::
አልጋ የሚባል ነገር በዚህ በአሜሪካ
እንኳን ሊተኛበት በእጅም አይነካ
ይታይ እንጂ በዓይን ተነጥፎ አምሮበት
መኝታ መሆኑ እስከሚያጠራጥር
ሰው በየሶፋው ነው ተዘርሮ የሚያድር::
የቤቱ አስቤዛ ጥሬ እቃው ተቀምጦ
በርገር በልቶ ያድራል ከነጭ ቤት ገዝቶ::
በሥራ ደካክመው ወንዱም ሆነ ሴቷ
ተገትራ ውላ ፍስስ ብሎ ሃሞቷ፤
የገዙት ጥሬ እቃ ቀኑ እያለፈበት
ትራሽ ነው ተብሎ ይጣላል ከመሬት::
በየትኛው አቅም ምን ጊዜ ይሠራ
ያው የስደት ኑሮ የግፍ የመከራ
ጡር የሚባል ነገር ባለንበት አገር
በሃሣብም የለ በአፍም አይነገር፣
እኔም እንደመጣሁ አሜሪካን አገር፤
ምግብ ጣይ ሲሉኝ
እኔ በእጄ አልጥልም ግፍ አለው እያልኩኝ
ለወገኔ አልከው ከቅርብ አይደለሁኝ
ስበላ ሣጣራ ምግቡ እንዳይባክን
ይኸው ተድበልብዬ ሁለት ሰው አክልኩኝ::



# ትምህርት

ዱሮ ያኔ ትምህርት ሲሰጥ
ለሕፃናት ትምህርት ቤት
ነበር በአለንጋ በመማታት
ፃፍ እያሉ እጅን ይዞ በመጐተት
ሳይጠነክር ያ ለጋ ጣት
እናት አባት በተራቸው
ልጁን ወስደው እቤታቸው
አጥና እያሉ በመቆጣት
አእምሮውን አስጨንቀው
እርሳስና ደብተር ሰጥተው፤
ዛሬ የታል የተማርከው
የፃፍክና ያነበብከው
ይኸው ደብተርህ ባዶ ነው
ለጨዋታ ነው የሄድከው
ብለው ልጁን አስፈራርተው
በአለንጋ ልብልብ አርገው
ደደብ ልጅ ነው ቅጣው ብለው
ይወስዱታል ወደዚያው
እንዲገርፈው አስተማሪው::
በልጅነት በለጋ ዕድሜው
ለምን ሳትፅፍ ዋልክ ብለው፤
የልጁን ሕሊናና መብት
እንደቀላል ነገር ቆጥረውት
ይሞክሩ ነበር ሊያስተምሩት::
አሁን ግን በሥልጣና

ያ ሁሉ ግርፊያ ቀረና
የልጁ ፍላጐት ተጢኖ፤
መማር ጀምሯል በፍላጐት
ደረጃው በሚፈቅድለት::

## ሞንቶሶሪ

እንደ ዕድሜአቸው ተመጥኖ
ሳይጨነቅ አእምሮአቸው
በሙዚቃ ተነቃቅተው
በጨዋታ ተደስተው፤
ከእለት ኑሮአቸው ጋር
የሚገናኝ ብዙ ነገር
ይማራሉ በመዝሙር::
እርስ በርስ ተረዳድተው
እሚማሩትን አውቀው
ተጠብቆ ሞራላቸው
የሰሙትን በጆሮአቸው
በእጅ ነክተው ፈትተው ገጥመው፤
ሞንቶሶሪ እንደሚለው
በሙከራ ተደጋግፈው
ተግባር ከቃል አጣጥመው
ሳይጐዱ በግርፋት
ተጠብቆ መብታቸው፤
የአለንጋን መልክ ሣያዩ
ተንበርክከው ሳይቆዩ
በውሎአቸው ተደስተው
ያድጋሉ እውቀት ቀስመው::



## የቱ ነው ሰው ማለት

በውስጡ እያደባ በአፉ የሚጫወት
እኔን ግራ ገባኝ የቱ ነው ሰው ማለት?
ወይስ እያበላህ ዞር ብሎ የሚያማህ
ዛሬ የኔ ነው ስትል ነገ የሚከዳህ፤
ጓደኛ ስትለው የሚሆንህ ጠላት
እስቲ እንነጋገር የቱ ነው ሰው ማለት?
እኔ አንዳንድ ጊዜ ጓደኛዬ እልና
የሆዴን በሙሉ ዘክዝኬ እነግርና
መፍትሔ ስጠብቅ ለነገርኩት ሚስጥር
ሲወራ እሰማለሁ ጉዳዬ ከመንደር::
እኔም ጓደኛዬን ምነው እባክህ ብለው
ችግሬን አዳምጠህ መፍትሔ ሳትሰጠው
ምን በደልኩህና ለአገር ነዛኸው?
ብዬ ብጠይቀው
ብሎ መለሰልኝ ለአንድ ሰው ብቻ ነው::
ሚስጥር ከሁለት ሰው ካለፈ ጨዋታው
ነገር መባከኑን እንደምን አጣኸው?
መፍትሔ ሳይሰጥህ ሚስጥር የሚያወጣው
የጓደኝነት እምነት መለኪያ ምንድነው?
ለጥያቄዬ መልስ ሃሣብ እፈልጋለሁ::
እናንተም ንገሩኝ ሰው ማለት የቱነው
ሰው ያለሰው መኖር እንደማይችል አውቀህ
ሰው ሆይ ለጓደኛህ ታማኝ ሁን እበክህ::

ሂሩት ሂሩት ብላት
ወይ አትልም ምን ገዷት
ሮጥ ብዬ ብይዛት፤
ዞር ስትል ደንግጣ (ተደናግጣ)
የማላውቀው የማያውቀኝ
ሰው ሆንኩበት ሰው ሆነብኝ
ደነገጠ ደነገጥኩኝ::
አንቺ ማነህ ብዬ ብለው
ጆኒ አብነት እባላለሁ
ብሎኝ እርፍ፣ በወንድ ድምፅ በጉርናናው
ረጋ ብዬ ቆሜ ባየው
ወንድ አይመስልም ፍፁም ሴት ነው::
የአይኑ ኩል የሚነገ
የቅንድቡ መስተካከል
ያስታውቃል መቀንደቡ በትክክል::
ተፈሽኗል ፀጉሩ
እስፒል ጫማ አርጓል በእግሩ::
የጆሮው ጌጥ የሎቲው
ወንድ አይመስልም ለሚያየው::
ፆታን ሽጦ መምሰል ሴት
ያስገርማል በእውነት::
በእናትነት የምመክርህ
በዚህ ቆንጆ ቁመናህ
ተፈጥሮ ባደለችህ፤
በፆታህ እንዃር በወንድነት
ሱሪ ለብሰህ ኮት (ከረባት)
ወገብህን ጠበቅ አርገህ



የወንድ ጫማ ተጫምተህ
በኩሩው ግርማ ሞገሥህ፤
ጅንስ ብትለብስ በትዝናና
ብትሠራ ብትማር ብትወጣ ብትወርድ
በቤት በውጭ በመንገድ
ምሣሌ ስትሆን ለጐረቤት
ለእናት ለአባት ያኮራል
ያሰኛል ልጅስ መውለድ እደዚህ ነው
ፀባይ ከእውቀት ያደለው::
ጥሩ ባህል ወግም አለህ
አያቶችህ ያቆዩልህ
አንዳንዴም በአረፍት ቀንህ
የጥበብ ልብስ እጀ ጠባብ ለብሰህ፤
ነጭ ጫማ ነጭ ሹራብ
ነጠላህን ብትደርብ
ያደርግሃል ቆንጆና ውብ::
ፈረንጆቹም ይዩት ወግህን
የሃገር ባህል ልብስህን::
ባህል እንዳለህ እሣያቸው
ለወገንህም ክብር ነው::
ይኸ ፀጉር መቆጣጠር
በሰው ባህል መወጣጠር
የራስን ንቆ የሌላን ማክበር
ያስመስላል የሌለን ባህልና አገር::

## መኖሪያ ፈቃድ

ፍቃድ አለት የመኖሪያ?
ባይታወርን ማሠቃያ::
አገር እያለን እንደሌለን
ወረቀት ፈቃድ የማይጠይቀን
በቂ ሆኖ መወለዳችን
መኖር ስችል ባገራችን ሥራ ፈጥረን
ከወገን ጋር ተንደላቀን
ብንጣላ ተቻችለን
ይቅር ተወው ተባብለን
ያጠፋውን እየቀጣን
መኖር ስንችል ተከባብረን ባገራችን
ምን ቀን አሰብን መሰደድን?
በሰው አገር መቸገርን
ቤት ስትፈልግ ሊዝ ፈርሞ
ቢል እያሉ ውሃ መብራት፤
አንድ ቀን ቢያልፍ ሳይከፈል
ፒናሊቲ ብለው ቅጣት!
አንዱን በሶስት አባዝተው
ይልኩታል በፖስታ ቤት
ካልከፈልከው ያንን ቅጣት
ውሃ የለ ስልክ መብራት
ያስወጡሃል በሳምንታት
ባገር ቢሆን ባደግንበት፤
ብትቸገር ባይኖርህ ብር
ጋሼ እከሌ ጊዜ ስጠኝ



አመጣለሁ ገንዘብ ሳገኝ
ብለህ ብትል ያምንሃል
እስከታገኝ ያኖርሃል
ያገር ልጅ ነው ያዝንልሃል::
አንድ ቀን ቢያፍ በዚህ አገር
የቤት ኪራይ ሳይከፈል፤
በቤት ሳትኖር ባካባቢው
ሰፋ አልጋ መኝታህን
ለሰራተኞች ንብረትህን፤
በመስኮት ከፎቅ ወርውረው
ያብቁታል ሰባብረው::
በዚህ ሁኔታ ብትኖርም
አንጼ ከወጣህ በስደት
ወረቀት ልያዝ በማለት
ቀኑን ሳታውቀው ሲያልፍ አመት፤
አንተም ሳታውቅ እንደዘበት
እድሜህ እየገፋ ሲያልቅ ጉልበት
አይቀርም ማዘን መፀፀት::
ስለዚህ በጊዜ ሰርተህ
አሁን በለጋ ዕድሜህ
አገርህን አልማ በርትተህ
ቤትህ ነውና ዞሮ መግቢያህ::

## ስደት

በተወለድንባት ባደግንባት ሰፈር
ጭቃ እያቦካን እንጀራ ስንጋግር፤
ባልና ሚስት ሆነን ቤት በአሸዋ ሠርተን
ሥኒ ከእሽክርክሪት፤ ከጭቃ ጀበና
እንደ እናቶቻችን እያፈላን ቡና፤
የውሸቱን ቡና እውነት አስመስለን
እትዬ እታፈራሁ፤ እትዬ በለጡ
እየተባባልን ቡና ቁርስ አቅርበን
በድንጋይ በርጩማ ባንድነት ተቀምጠን
ወሬ እያወራን ዘፈን እየዘፈንን ፤
መንደር ተሰብስበን ጠዋትና ማታ
እንጫወት ነበር እቃእቃ ጨዋታ።
የዛሬው ይመጣል ብለን መቼ አሰብን
ያችም ርቀት ሆና ከአዲስ አበባ ሐረር
ቫኬሽን ስንሄድ እንሳቀስ ነበር
ዛሬ እዚህ ልንደርስ ባህርን ተሻግረን።

## ማሙሽዬ

የመኖሪያ ፈቃዴ
አቆራረጠኝ ከወገን ከዘመዴ፤
ኑሮዬ የቁም እስር ሆኖብኝ
ወጥቶ መግባት አቅቶኝ
አገሬን በሃሣብ እንጂ ሳላየው በውን
ጉረቤት ጓደኞቼ ናፍቀውኝ፤



በስልክ አይወጣ ናፍቆት
እንደራስ አይሆን መልእክት
ሰው ብልክ ሣሙልኝ ብዬ
የቀረው ልጄን ከቤት ከቀዬ
ለአይኖቼ እይታ የሚናፍቀኝ ማሙሽዬ፤
የሄዱት ሁሉ ቢስሙልኝ
ናፍቆቱ ጭራሽ ባሰብኝ
አየነው ብለው ሲነግሩኝ፤
ውስጤ ይረበሽና
ስልክ ደውዬ እንደገና
ማሙሽ እንዴት ነህ ደህና ነህ ስለው
ብቸኝነቱን ሲያሰበው
እረ መቼ ነው የምመጣው
በናፍቆት እዚህ ተጉዳሁ
ብሎ ይለኛል የደላው
መውጪያ አጥተን የመጣነው
ችግሬን እንዴት ላስረዳው?
መውጪያ መውረጃ እንዳጣሁ፤
አገር ቤት ያለው ወደዚህ
እዚህ ያለነው ወደዚያ
አገርን ትተን እንደዋዛ
ካደኩባት ከኖርኩባት እትብቴ ከተቀበረባት
አፈር ፈጭቼ፤ ጭካ አቡክቼ ካደኩባት እምዬ
ሕልም ሆኖ ሲታየኝ መመለሻዬ
ምን አሥቦ ይሆን ያወጣኝ እግሬ
ከምወዳት ከውድ ሐገሬ።

## ጥላሁን ገሠሠ

ጥላሁን ገሠሠ ቀደምቱ አርቲስት
ሞያውን አክባሪ የኪነት አባት
ለደስታ ለፍቅር ለሃገር ወገን ሕብረት
ግጥምህ አመቺ ነው ድምፅህ አዳሽ ሕይወት::
ጥልዬ ዘፈንህ ግጥምህ ከድምፅህ
የተዋጣለት ነው እንከንም የለህ::
በሃዘን ተቆራምዶ የተጨነቀ ሰው
ዜማህን ሲሰማ ይድናል አእምሮው::
ቁጭ ብዬ ስሰማው ዜማህ ሲንቆረቆር
ለጆሮዬ ጣዕም ለአእምሮዬ ደስታ
ሕይወትን በመዝራት ለመላ አካላቴ
የሚሠማኝ ሕመም ይጠፋል ከፊቴ::
ግጥምና ዜማው ተጣጥሞ ሳየው
ድንቅ ይሆንብኛል ጥላሁን ተስጥዎው::
ትዝ ይለኛል ዱሮ ሳለሁ በልጅነት
ለጥላሁን ዘፈን ሕዝቡ ያለው ስሜት::
እረ ይሻልሻል እረ ይሻልሻል
አበበ ቢቂላ ጀግናው ያገባሻል
ጥላሁን ገሠሠ ዘፍኖ ይድርሻል
እረ ይሻልሻል አንቺስ ታድለሻል ::
ትዝታው አለብኝ ሰፈር ስንዘፍነው
ት/ቤት ስንሄድ ሰርግ ስንጫወት::
መቼ ይረሳና ፍቅር ቁምነገሩ
በአገር ልጅ ተወዶ ተከብሮ መኖሩ::
ዝንባሌህ ሆኖ የአምላክ ሥጦታህ



አርቲስትና ዶክተር ለመባል በቃህ
ገና ስትጀምር የነበረው ድምፅህ፤
ምን ዕድሜ ቢጨምር ሕመም ቢከተልም
ምንጊዜም አዲስ ነው ድምፅህ አይቀየርም::
ጭራሽ የድምፅህ ቃና አምሮና ጨምሮ
በዳላስ ከተማ አየንህ ዘንድሮ::
ራዕዩን ተናግሮ ውይይት ሲጀምር
ለዳላስ ነዋሪ (ወገኑ) ሃሣቡን በማቅረብ
ሕልሙ እንዲተረጐም በውን በተግባር
ለድሃ ወገኑ ሐውልት ለማኖር፤
ባለው ቅርሱና በወገን እርዳታ
ጅምሩ ተሣክቷል ራዕዩም እውን ሆኗል
ስሙን ተክሎ ለሃገር ጥላሁን ያኮራል::
ለወገን ተቆርቋሪ አሣቢ ለሃገር
የኪነቱ ባለቤት ድምፃዊው ዶክተር::

## አለባቸው ተካ

ለሲቱን በባትሪ ቀኑን በብርሃን
ወገኑን ለመርዳት ቀን ከሌት ሲተጋ፤
የድሃ ወገኑን ጉዳት በመረዳት
ያገሩን ልጅ ብሶት ለወገን በመንገር
ስንቱን ኢትዮጵያዊ አወጣ ከችግር::
ከጥንት ጀምሮ ታሪክ የሠሩትን
ተረስተው በማጀት ከቤት የቀሩትን፤
ታሪክ በመመርመር ዱዶ በየጓዳው
እንዳይቀበሩ ከነታሪካቸው

አለባቸው ተካ ኢፋ አወጣቸው።
ወጣት እንዲደራጅ አንድ ሆኖ በሕብረት
ሸክም ሆኖ እንዳይቀር ለወላጅ ለሃገር
በሉላሉስ ፀባይ ተስፋ ቆርጦ እንዳይቀር
እያስተባበረ መንግሥትና ኢንቨስተር፤
የሰው እጅ እንዳያይ ሆድ እንዳይብሰው
እንደዝንባሌው እንደ ችሎታው
ባለ ተስፋ አረገው ሥራ አስተማረው
ጧሪ የሌላቸው ሽማግሌ አሮጊት
በየሜዳው ወድቀው ጠቁረው ሲያገኛቸው፤
ወደ ሚዲያ ያመጣቸውና
እንባውን ያፈሳል ወገኑን ልመና
እሱ መቼ ይችላል ሩህሩህ ነው ፍጥረቱ
ትልቅ ታሪክ ሠራ ሳለ በሕይወቱ።

2002

## እውን ሲሆን ሞቱ

እውን ሲሆን ጉዞው
ዳግም ላይመለስ እስከመጨረሻው፤
ልጆች ጓደኞቹን ሳይሰነባበት
እንደ ወጣ ሊቀር አለባቸው ድንገት
ለውድ ጓደኞቹ በጣም ለሚቀርቡት
መሄዱ ነው ሳይል ሳይናገር መልእክት
የልጆቹን እናት በድንገት ሊለያት
ዳግም ላይመለስ አለምን ላያያት፤
የብዙ አመት ሕልሙ ሥራና እቅድ



ተበትኖ ሊቀር በጅማ መንገድ
ተስፋቸው ሲጨልም፣
ይመጣል እያሉ ቤተሰብ ዘመድ።
ያ ብዙ የሠራበት ቴሌቪዥን ጣቢያው
ይመለሳል ሲሉ በውን በሕይወቱ
እስክሪኑን ሲያዩት ነብሱ ተለይቶ
የሚሰማቸውን አልገምትም ከቶ።
ወገኑን ለመረዳት ሲዞር አገር ላገር
ሲለፋ ሲደክም ሰው ለመሆን ሲጥር
ያላሰበው መጥቶ ከቤቱ ሲያወጣው
ምንም ሳይጠረጥር ለሞቱ ሳይመስለው
እንደወጣ ቀረ ተጣደፈ ጉዞው።
ወንድሜ አለባቸው እስቲ ልጠይቅህ
መንገዱ እንዴት ነበር የዘላለም ቤትህ?
ተድላ ደስታ አለ ወይ? እንዴት ተቀበሉህ
ጥለኸን ስትሄድ ወገን ሲጠብቅህ።

2006

## ሴት እኮ እናትም ናት

በከተማም ሆነ በገጠር ስታያት
በወንድነት ስሜት ብቻ አትመልከታት
በችግሯ እርዳት ሴት እኮ እናትም ናት።
ከአንተ እኩል መቋቋም አቅም ባይፈቅድላት
ከርህርሄ ውጭ ጉልበት አታሣያት
ስሜታዊ አትሁን ድንገት ስታገኛት
ስትደክም ደግፋት ሴት እህትህምናት።

በወንድነት ስሜት በቻ አትመልከታት
ፍቃዷን ሣትጠይቅ ፍላጐት ሳይኖራት
የመድፈር ሙከራ ከቶ አታድርግባት!
በእህቴ ላይ ቢደርስ ብለህ አስብላት።
መቋቋም ባትችል ስሜት ቢያሸንፍህ
ቆም ብለህ አስብ ፍላጐት አይግዛህ።
በወገኔ ቢደርስ በአክስት በሚስቴ
ተደፍራ በወንዶች ቢነካ ስሜቴ
ምንድነው የምሆነው እኔ በእኔነቴ?
ሞራሏ ተነክቶ ስትጐዳ እህቴ ሲናጋብኝ ቤቴ!
ብለህ አስብላት ለዚያች ለወገንህ
እህትህ ባትሆን የሥጋ ዘመድህ
ማመዛዘን ይወቅ ሕሊናና አዕምሮህ
የስሜት ተገዢ አይሁን ጭንቅላትህ።
አይተህ ካፈቀርካት በእውነተኛ ፍቅር
ቀርበህ አነጋግራት መደፈሯ ይቅር።
ግን ትዳርን ትተህ ወዲያ ወዲህ እያየህ
ተስፋ ቢስ አታርጋት አንተም እህት አለህ
ትዳርህን ትተህ በትርፍ አትጫወት
ያንተንስ ማን ያውቃል አንዱ ቢወስድብህ
አተርፋለሁ ብለህ ዋናው ቢጠፋብህ
እዚያም እዚያም ቢሉት ትርፉ በሽታ ነው
አምላክ የፈቀደው አንድ ለአንድ ነው።



# ጭቁኑ ውሻ ችሎ ማደር

ያ ጭቁኑ ውሻ አገር ቤት ያለው
የሰው ልጆች ወዳጅ፣ የቤት አንበሳው
ዝናብ እና ፀሐይ የማይለየው
እደጃፍ ላይ ታስሮ የሚያላዝነው፤
ምግብ ከመሬት ላይ የሚጣልለት
ታማኙ አገልጋይ ለሰው ቀን ከሌት
ጌቶቹ ቀማምሰው ካልተረፋቸው
ጠብ አይልለትም ያ - ወዳጃቸው
ያሙን ይውላታል እያየ አይናቸው።
አንዳንዴም ምግብ ካልተበላሸ
ካልሻገተና ጣዕም ካልለወጠ
ግፍ ሠራ ይባላል ለውሻ የሠጠ።
እንዲህም ሆኖ ያ - ገራ ገር
አገር ቤት ያለው ችሎ ማደር
ጌታው ተኝቶ ሃሣቡን ሲጥል፤
ንብረት ሲጠብቅ ሳይተኛ ያድራል።
ታማኝ አገልጋይ ለባለቤቱ
ሌባ እንዳይዘርፈው እንዳይጐድል ሃብቱ፤
አንዳንዴም ሲገልፅ ሰውን መውደዱን
በፍቅር እያየ ባለቤቶቹን፤
ታሥሮ ሲፈታ ሲያገኝ ነፃነት
ወደቤት ሲሮጥ ቁጭ ወዳሉበት
ውጣ ይሉታል ልክ እንደጠላት።
መች በዚህ ያልቃል የችሎ ታሪክ
የሚያየው የለም ጤናው ሲታወክ።
በአመት ማስከተብ ችግር መስሏቸው

አንጀቷ ተጣብቆ ፊቷ ይገርጣ እንጂ
እናት በልቷ አትውልም ሳይጠግቡ ልጆች።
ችግሯን በውስጧ ሸፍና በግሏ
ለልጆቿ ጋሻ ዘውድ ናት ለባሏ።

## አባት ለልጁ

መቼም ልጅ ነው ለእናት ለአባት
በሕይወት ሆነ ደራሽ በሞት
በችግር በበሽታ እራሷን ጉድቷ ተንገላታ
ሴት ልጅ ሩህሩህ ነች ለአባቷ።
ታዲያ አድጋ ይህን ለምትሠራ
አባት ምንም ሳይራራ፤
በሰይጣን ተልዕኮ መሪነት
ልጅን መቀጨት በልጅነት።
አባት ለልጁ መሆን ሲገባው አጋር
ልጅን እንደባዳ መድፈር
ይታያል በዚህ አገር።
አሠቃቂ ነው በኛ ባህል
ነውር ፀያፍ ነው በሌላውም
ይህንን ለመፃፍ ያስገደደኝ፤
ባለፈው ባገራችን የተፈፀመው ዘግናኝ ነገር
ሆኖብኝ ነው የአደባባይ ሚስጥር
አባት የ12 አመት ልጁን በመድፈር
እቤት አውሏት ከሰፈር፤
የኅብረተሰቡን አእምሮ ጉድቶ
ይኸው ይገኛል ወህኒ ገብቶ።



አትፅናና እናት የላት አይዘሽ የሚላት
ሁኔታው ጨቅላ አእምሮዋን በጥብጧት
ስትሰቃይ በእንጀራ እናት
ሰው በሐሜት ሲኮንናት
መቆም መቀመጥ አቅቷት፤
የወደፊቷን ስታሰበው
ከትምህርት ገበታዋ ተለይታ
እንቅልፍ ሲነሣት ቀን ማታ
የአባቷ ክፋት እየታያት
ድርጊቱ እንደጥላ ሲከተላት
ቁጭት ሲያንገበግባት
አእምሮዋ ሲወጠር በጭንቀት
የሷ መኖር ትርጉም ሲያጣባት፤
ቢሆንባት የሚቀፍ ለጆሮ
የማይጥም ለአእምሮ
በምድር የምትኖረው ኑሮ
መረጠች ለማጥፋት ሕይወቷን
ደግሞ ላለማየት አባቷን።
እኔ ይህንን የምፅፈው
ሰው ስሜቱን እንዲቆጣጠር ነው።

## ያዘነ ልብ

ፀፀት አይሉት ቁጭት
ባዶነቱ ሃዘኑን ጨምሮት
ማልቀስ አይሉት መንሰቅሰቅ
ሁሉም ሳያልፍ ከልክ

ብቃትት ላስተካክለው
ጭራሽ እራሱን ጉዳሁ
ላይመለስ ያለፈው፤
ሆኖብኝ የእግር እሣት
ለበለበኝ ቀን ከሌት::
ክብሬን አሣልፌ ስሰጠው
እንደሚያፈቅረኝ ነበር የማውቀው::
ፍቅሩ ቀጣይ ነው ብዬ
ለዘመዶቼ አማክሬ
ለጓደኞቼ ነግሬ፤
አባቴ ያለውን አሟጦ
ትዳር መያዜን መርጦ
ወንድም እህቶቼን ሰብስቦ
በዘመድ አዝማድ ተከቦ፤
ባህል ስለሆነ ማዕረግ
ልጅን መዳሩ በወግ፤
ጠላ ተጠምቆ ጠጅ ተጥሎ
የጥሪ ወረቀት ተበትኖ
ዘፋኝ ፎቶ አንሺ መጥቶ
ሙሽሪዬ ሙሽራው
ቀኑ የናንተ ነው ተብለን
ተጨፍሮ ተዘፍኖ፤
የሽማግሌና ቤተሰብ ጉልበት ስመን በክብር
ሠርጋችን የሚያምር ነበር
ሦስት ጉልቻ ኑሮ ስንጀምር
ባንድ ጉጆ ባንድ ጣሪያ ሥር ወስነን ስንኖር::
የኋላ ኋላ ስንቆይ



እያደር እወጣው ድብቁን ፀባይ
ሃብት ሲመጣ ነዋይ
ንቀት አመጣ በኔው ላይ፤
የልጅ የቤትን ጉዳይ
ሃሜቱን ጥሎ በኔ ላይ፤
መሆን ጀመረ ዘበናይ::
እኔነቴን የሠጠሁት
መቀነቴን የፈታሁለት
ሆኖኝ ተገኘ ክፉ ጠላት::
ይህንን ግጥም የፃፍኩት
አንዷ ትዳር ያማረራት
ብትማፀነኝ ነው ድንገት
ስሟ ይገለፅ ብላት
እንባ እየተናነቃት
ስሟን መናገር አቃታት::

## ምሬት

ያለ ምክንያት ማማረር
አለመመቸት ነው ለእግዚአብሔር
አምላክ በሰጠን አለመርካት
ባቅም መኖርን አለማወቅ
በሌለን ነገር መጨነቅ
ያደርሳል ለትልቅ ክስረት::
አንድ ቀን ማታ ቤቴ ስገባ
ውስጤ ተጨንቆ ሆዴ ባባ::
ቤቴ እንደበረዶ ቀዘቀዘኝ
አትቀሚ አትቀመጪ አትግቢ ሂጂ

የሚል መልእት ከየግድግዳው
ከጣሪያውና ከምንጣፉ
በአንድ ላይ ለፈለፉ
ተባብረው እኔን ሊያጠፉ።
እኔም ሳይ ሁኔታቸውን
ቢጋራ መወሰናቸውን፤
ጭቅጭቃቸው (ንግግራቸው) ለበጐ መስሎኝ
ቁልፌን ይገፍ ወጣሁኝ።
ሞክሬ በእግሬ ለመንዝ
ብርዱ ሲገባ ካንጀቱ
ደግሞ ተመለስኩ ወደ ቤቱ።
አሁንም ቆሜ ሳይ ውስጡን
የተወረረ መሆኑን
ብቸኝነቱን ጠላሁት
አገሬን ቤቱን አስብኩት
ያን መኖሪያ ካርድ ረገምኩት።
ብቻ በዚያችው ቅፅበት
ጉድ ነው ስንቱን አሰብኩት?
ይህንን እያሰላሰልኩ
ወዲያው ለመውጣት አሠብኩ
ሞቃት ጫማና ኮት ደረብኩ።
አሁንም በእግሬ መንገዱን
ይገፍ ስሄድ ዳርዳሩን፤
በሃማብ ፈረስ ነጉድኩኝ
ጆሮዬን ብርድ ሲጠብሰኝ
ንፋስ ሲያወዛውዘኝ፤
ሌላ ሃሣብ መጣ በአእምሮዬ



ይህም ሁሉ ሆኖ በዚያው ሰአት
በቁሜ ስቃዥ ስቀባጥር
መኪናዬ ውስጥ ገብቼ
መንዳት ጀመርኩ ወደ ልጆቼ።
መቼም ያደቆነ ሰይጣን
አይለቅም ሳያቀስስ እንዲሉ
ሃሣቦቹና ምሬቶቼ በሙሉ
ከኔው ጋር ነበሩ እንዳሉ።
እነሱን ሣወጣ ሳወርድ
መኪናዬ ወጣች ከመንገድ።
ስነቃ ከሃሣብ ፈረስ
አየሁ ግንቡ ሲደረመስ
ተከብቤ በፖሊስ በአምቡላንስ
ፍርጃ ቤት አይውልም አበው ሲሉ ብሰማም
የኔ ደግሞ በውድቅት ቀኑን ውሎ በሰላም
ፍርጃው አለኝ ቤት አላድርም
ብሎ አወጣኝ እንደምንም።
እንደዚያም ሆኖ ከአደጋው
እግዚአብሔር ነፍሴን አዳነው።
የአደጋው አስፈከፊነት ሲታይ
አምላክ ባያየኝ ከላይ
ባይደግፈኝ በክንፎቹ ባይከልለኝ
አላፊ ሟች ነበርኩኝ
አልተውሽም አለቅሽም ያለኝ
ከጥንቱም ለአባቶቼ ቃል የገባልኝ
እግዚአብሔር ከለላ ሆነኝ
ምህረቱን ሊያስተምረኝ።

በሣምንት ሁለት ቀን ያቀርባል ዝግጅት።
እኛም ተሯሩጠን ብለን ቀና ደፋ
ለሰው ጆሮ እንዲደርስ በገሃድ በኢፋ
ሁሉም ተቀናብሮ በእሁድ ሬዲዮአችን
እናቀርበዋለን በሙዚቃ አጅበን።
እናንተም ወገኖቻችን
የቀድሞም አባሎቻችን፤
ላኩልን ከየኪሣችሁ
አስደሳች ዜና ካላችሁ
ገንዘብም ቢሆን አይሷችሁ።
ይህ ድርታችን የተመሰረተው
የዛሬ ሰባት አመት ነው
በነዚሁ አመታት የተሰራው ሥራ
ይህ ነው አይባልም ተጠቃሚው ያውራ።

ከወ/ሮ ሙሉመቤት ገ/ዮሐንስ
የድርጅቱ ሕዝብ ግንኙነት

## እንዳስተዋልኳቸው

ማሩ ግሮሰሪ ቬሻ ውብ እንጀራ
በደስታ ብችግ በሞት በመከራ፤
የሚያደርጉት ሩጫ ከሃገር ልጅ ጋራ
ውለታቸው በዛ አያልቅም ቢወራ።
አንድ ችግር ቢደርስ በአካባቢያችን
ሮጦ አይዞህ በማለት ወጪ ለመሸፈን
የሚያደርጉት ሥራ ያኮራል ወገንን።
አበባ ግሮሰሪ ሴቷ ነጋዴአችን
በተጠራችበት ፈጥና ደራሻችን፤



አንድ ወገን ቢጐዳ እንባ እየቀደማት
ምግብና ገንዘብ ያላትን በመስጠት
ሁሉን ነገር ትታ በቦታው በመገኘት
መልካም ልብ ያላት ባለ ውለታ ናት።
ቴዲ መርካቶና መስፍን ታክሴ ከረጁ
ምንጊዜም ለወገን ደራሽና ረጄ
ለሃገር ልጅ መጐዳት እንደዚህ ነው እንጄ!
ከረጂ የቤተሰብ የምግብ አገልግሎት
ምጊዜም ለድግሥ አዳራሽ በመስጠት፤
ወገን ለማስደሰት እንዲሁም ለማዝናናት
ለችግርም ደራሽ ለመከራ ለሞት
አገልግሎት ሰጪ በፈቃደኝነት።
አዲስ አባ ሆቴል ሙሴ የባህል ስቶር
ለወገን ተቆርቋሪ ደራሽ ለሰው ችግር.
ኢትዮ ቢውቲ ሙሴ የውበት ሣሎን
እርዳታቸው ሰፊ ለሃገር ልጅ ለወገን።
ቢክሪ ምግብና ስታር ግሮሰሪ
በበጐ ሥራቸው አገር ወገን አኩሪ።
ሲቲ ካፌ ተስፋ የኬኩ ባለቤት
ስመ ጥር ነጋዴ በየደረሰበት
ጥሩ አስተዋፅዖ አለው ችግር በሰማበት።
ላሊበል ሆቴል ቹቹ ግሮሰሪ
የጥቃት መከታ፣ ለሰው ተቆርቋሪ!
ወገን ሲጐዳና ሲደርስበት ችግር
ቀድሞ በመገኘት ሰው በማስተባበር
ጥሩ ድርሻ አላቸው ለወገን ለሃገር።
ሂሩት እንጀራና ጐጃ ሆቴል ጊዮን

ለችግር ደራሽች የሃገር ልጅ ለወገን።
የእታፈራሁ ስቶር እንዲሁም መዲና
በትብብራቸው መቼ ይራሱና?!
ደስታ ሆቴልና አይቤክስ
ለተከፋው ደራሽ፣ ላነሳው ለጋስ፤
ሥራ ላጣው ሁሌ ስራ በመስጠት
ጥሩ ትብብር ነው ወገን ማስጠጋት።
ጤናዬ እንጀራና ውዳሴና አዋሽ
ስለ ወገን ችግር ጠያቂና አስታዋሽ።
ወንድሜ አስማማው ሼብሮን ጋዝ ባለቤት
ወገንን በመቅጠር በእምነት በቅንነት፤
እንደ ወንድማማች አብሮቸው በመሥራት
የባለቤትነት ስሜት ሳይኖርበት
ብዙ ወገን ረድቷል መመስገን አለበት።
ሰቨን ኢለቨን (7[11]) ያለው ዮናስ ወንድማችን
የወገን አልኝታ፣ፈጥኖ ደራሻችን፤
የተቸገረውን ሥራ እየቀጠረ
ስንቱን ያገሩን ልጅ ከችግር ሰወረ?!
ሣፋሪ የገንዘብ መላኪያ ድርጅት
በችግር ተባባሪ በደስታና በሞት።
አርቲስት እህታችን ድምፀ ጥሩዋ ሂሩት
ባናቱም የሷ ነው ቀንጆ የክትፎ ቤት፤
ፈንድ ሬዚንግ ቢኖር ሳትጠይቅ ክፍያ
ወገን ታዝናናለች ባላት መልካም ሞያ።
የባዜ ሱቅና የአባቡ ድርጅት
መቼም ቢጠየቁ ወገንን ለመርዳት
ፈጥኖ በመመለስ እርዳታ በመስጠት፤



ከወገን ጐን በመቆም ቀንም ሆነ ማታ
ተባባሪ ናቸው በየትኛውም ቦታ።
አብዲ ልብስ ሰፌት የሠሚያ ሱቅ
ምንጊዜም ለችግር ለሃገር ልጅ ጭንቅ፤
በመሽቆጥቆጥና እንግዳ ተቀብሎ ሥራ በማስገባት
የሚያደርጉት ተግባር አለው ትልቅ ግምት።
የዳዊት ክትፎ ቤት መስፍንና ፀሐይ
የአገር ልጅ ሲጨነቅ ሲያጋጥመው ችግር፤
አይዞህ በርታ ብለው በመስጠት ምክር
ብዙ ሜና አላቸው ለወገን ለሃገር።
የሃገሬን ነጋዴዎች እንደስተዋልኳቸው
ለወገን ለሃገር ፈጥኖ ደራሽ ናቸው።
አንድ ወገን በድንገት ቢሞት በአካባቢው
ወጡ ጥሬ ዕቃው እንጀራና ዳቦው፤
ለአስተዛዛኞቹ እንዲሁም ለቀባሪው
የሚዘጋጅቸው በምግብ ቤቶች ነው።
እንዲሁም ኀደኛ ዘመድ የሌለው
ታሞ ቢተኛና ቢውል ከአልጋው፤
እርዳታ ቢጠየቅ ለማስታመሚያው
ባለ በሌለ አቅም ገንዘብ አሰባሰበው
የግል ንግዳቸውን ወደጐን አድርገው
ሱቅ የሚወጣውን ደንበኛ አሣምነው
ከየኪሳቸውም ያለውን ጨምረው
የወገኔ ችግር ያው የኔ ነው ብለው
ለነብስ ይደርሳሉ ከሁላችን ቀድመው።
እነዚህ ወገኖች እንደዚህ ካኮሩን
ለወገኖቻችን እናድላ ሁላችን።

የወር የሣምንቱ የቀን አስጌዛችን
ከወገን ሰቅ ይሁን ሁሉም ገበያችን።
እስቲ እንመልከት ሌሎች አገሮችን
አረብም ከአረብ ነው ሕድም ከሕንድ ነው
ኤዢያም ከወገኑ ቻይናም ከቻይናው፤
እኛም ለኛ ብለን እንጥቀም ወገንን
ወገን ለወገን ነው እንማር ሕብረትን።
እንግዲህ ወገኖቼ፣ የምትታወቁ በመልካም ሥራችሁ
ድንገት ተዘንግቶ ባይወጣ ስማችሁ
ከይቅርታዬ ጋር ምስጋና ይድረሳችሁ።
እኔም በዚህች ጽሑፍ ብዙውን ባልገልፅም
የአገሬን ነጋዴዎች ሳላደንቅ አላልፍም።

## ሴቷ ወገናችን

በሰው ባህል ተደልላ
የራሷን ጥላ ወደኋላ
አጭር ቲሸርትና ቁምጣ
የፓንት ያህል በላይዋ ጥላ
ባዶ ሆኖ ተራቁቶ አካሏ
እምብርቷ እስኪታይ ጌጥ አጊጣ
ትታያለች ተገላልጣ።
ጥቁር ነች ነጭ ተብላ
ያሳዝናል አዋዋሏ ሳትታወቅ በወገኗ
ድሮ ያኔ በኛ ዘመን
ባቷ ነበር የሴት ጌጧ
ፀጉሯ ነበር ሐር ጉንጉን
የሚያምርበት ስትጎነጉን።



ዛሬ ድብቅ አካልን እንብርትና ጡትን
ለሰዎች አይን አጋልጠን
ወዲያ ጥለን ባህላችንን
ምነው እኛስ ወደብ ሆንን
ማራገፊያ የሌሎች ባህልን።
እየዞሩ መጠጣቱ ማጨሱና መዝናናቱ
ጫት መቃሙ ድራግ መጋቱ
አላማን ሥቶ መገኘቱ
አእምሮን ማወክ ማናጋቱ
ወግ አይደለም ተይው እቱ።
ይልቅ እኔ የምመክርሽ
ይህን ሁሉ እርግፍ አርገሽ
ኩሪ በባህልሽ አጊጪ በጥበብሽ።
በእናትሽ ባህል በወገንሽ
ቀንጆ ጥበብ አስፍተሽ
ነጠላሽን ደረብ አርገሽ፤
አርጊው የእጅ አምባርሽን
አጥልቂው የእግር አልቦሽን
ውበት የሚሰጥሽን።
ባህል እንዳለሽ አሣያቸው
ለወገንሽ ክብር ነው።
ይሰራ ፀጉርሽ ሹርባ
ገላሽ ይታጠን በወይባ።
ሹሩባው ይነስነስ በአደስ
የእናትሽ ባህል እንዲታደስ፤
ደሃ አደግ እንዳትመስያቸው
ባህል እንዳለሽ ንገሪያቸው
ለወገንሽም ኩራት ነው።



ገጣሚዋ
ሙሉመቤት ዮሐንስ ወ/ማርያም

መታሰቢያነቱ

መታሰቢያነቱ በፍቅርና በመልካም ሥነ-ምግባር
ላሳደጉኝ ወላጆቼ እና ለቤተሰቦቼ ይሆን
ዘንድ ሳበረክት በታላቅ ደስታ ነው።